# ይህን መጽሐፍ ለማጥናት የሚረዱ መንገዶች

ይህ 1ዮሐንስ መጽሐፍ በግላቸው ማጥናት ለሚፈልጉ ሰዎች የተዘጋጀ ነው። በመሆኑም በቡድኑ ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ሰው በትምህርቱና በውይይቱ ተሳታፊ እንዲሆን ለማድረግ የተጻፈ ነው። ውይይቱ ቀጣይነት እንዲኖረው መሪ ያስፈልግሃል። ታዲያ ይህ መሪ አስተማሪ ሳይሆን ሰዎች ወደ ውይይቱ እንዲገቡ አስፈላጊውን ሁሉ የሚያደርግ መሆን አለበት።

<u>መሪው ማድረግ የሚያስፈልጋቸው ሀሳቦች ከዚህ በታች ቀርበዋል፦</u>

1. የቡድኑ ጊዜ ከመድረሱ አስቀድመህ ትምህርቱን በማጥናት ራስህን አዘጋጅ። ይህንን ማድረግህ ለቡድኑ አባላት ግልጽ ያልሆኑ ነገሮች ሲፈጠሩ ገለጻ እንድትሰጥ ይረዳሃል። በቅድሚያ ስትዘጋጅ ለትምህርቱ እንግዳ አትሆንም።
2. በእያንዳንዱ ሳምንት <u>ድምጽህን ከፍ አድርገህ መግቢያዎቹን</u> አንብብ።
3. በሁሉም ትምህርት ላይ የቡድኑን አባላት በሙሉ የሚያሳትፍ ሥራ መሥራት አለብህ። አንድ ሰው ክፍሉን በሚያነብበት ጊዜ አንተ በምትፈልገው ቦታ ላይ ሁሉም ሰው በማንበብ እንዲሳተፍ አድርግ።
4. የክፍሉን ሀሳብ ለማጉላት የሚጠየቁ ጥያቄዎች ሰፋ ያለ ውይይት የሚደረግባቸው ጥያቄዎች አይደሉም። ይልቁን እነዚህ ጥያቄዎች የመጽሐፉ ክፍል ምን ለማለት እንደፈለገ ለማጉላት ነው የተጠቀሙት። ምናልባት የመጽሐፉን ክፍል ደጋግማችሁ ማንበብ ሊያስፈልጋችሁ ይችላል። ይህ አስፈላጊ ነው። መልሶቹ በሙሉ በክፍሉ ሀሳብ የተመሠረቱ ናቸው።
5. ምናልባት ትምህርቱ ረጅም የሚሆን ከሆነ ለሁለት ልትከፍል ትችላለህ።